# ይድረስ የቄሮንና የጃዋርን ፍቅር በቅጡ ላልያዛችሁት ወገኖቼ!
## ደረሰ ትንቢቱ (ከአዲስ አበባ)

እውነት ነው - ፍቅር ዕውር ነው። በፍቅር የታወረ ሰው ወይም ፍጡር በፍቅር ካሳወረው አካል ሌላ አያውቅም፤ ሊያውቅም አይችልም። በአማርኛ ፍቅርን ለመግለጽ የማስታውሰው ሌላ ቃል "መውደድ" ነው - በዚህ ላይ የምጨምረው ብዙም የለም፤ ስለጥላቻና ነገር ቢሆን ብዙ ቃል በታወሰኝ - ያለን ብቸኛ አንጡራ ሀብት ቂም በቀልና ጥላቻ እንዲሁም መሰዳደብ ነውና፤ ስለፍቅርና ውዴታ እናንተም ቃል ፈልጉ - ብዙም አታገኙም፤ ስንገርም! በእንግሊዝኛ ግን ብዙ አሉ። ለምሣሌ - love, agape, infatuation, affection, passion, ….ሌሎችም ይኖራሉ፤ አሉም።

ስለፍቅር ፍልስፍና ውስጥ አልገባም። እኔ አሁን የማወራው በእንግሊዝኛው infatuation ስለሚባለውበአማርኛ የወረት ፍቅር በሚል ልንገልጸው ስለምንችለው የሆይ ሆይታ ፍቅር ነው። ይህ ዓይነቱ ፍቅር መነሻው ደምባራ ስሜት እንጂ ተጨባጭ ምክንያት አይደለም። በዘር መቆላለፍ ወይም በትውልድ ሐረግ ወይም በዝምድና ወይም በጥቅም በተሳሰረ የወል ዓላማ መደጋገፍ ይመሠረትና እስከመጨረሻው የጥፋት ጥግ ድረስ አብሮ ሊያስጉዝ የሚችል የአመክንዮ ሳይሆን የግለት ቁርኝት ነው - የወረት ፍቅር። Calf's loveም ይሉታል ፈረንጆቹ። እውነትም እናቷንና ጨሌ ሳታገኝ ውላ እንደተፈታች ጥጃ በባዶ ሜዳ የሚያስፈነጭ ስሜት ወለድ ፍቅር!የሚመለከትሽን ሁሉ እስከዶቃ ማሰሪያሽ እነግርሻለሁና ወረድ ብለሽ ጠብቂኝ፡-

በሚሌኒየም የተካሄደውን የልዑለ እምልዑላን ኦቦ ፊልድ ማርሻል የኦሮሚያ በፊት ድብቅ አሁን ግልጽ ፕሬዝደንት የጃዋር መሀመድን እግ የሚያስደምም መስተንግዶ አየሁት። የወሬየ መነሻ ቅናትም ሆነ ምቀኝነት አይደለም - በጭራሽ። ከሀገር ጎልውናና አነስ ሲልም ከፕሮቶኮል ጋር ይያያዛል። ጃዋር መሀመድ በስደት "አንተ ማነህ?" ተብሎ ሳይጠየቅ ተራ ስደተኛ ያልነበረውን ያህል እዚህች ሊያርዷት ቢላዎ ሲስሉላት በምትስቅ ሀገር አቶ ለማን ጨምሮ ከፍተኛ የ"ፌዴራል"ና የክልል ባለሥልጣናት እየተሽቆጠቆጡ - ሊያውም ብዙ አስደግድጎ እጅግም ዘግይቶ ሲገባና ታዳሚዎች

በታላቅ ደስታ ምድርን ቃጤ ሲያደርጉ ሳይ የሀገራችን ትንሣኤ ኩልል ብሎ ታየኝ - ከዚያማ የባንዲራው ነገር፣ የጬቤ ረገጣው ነገር፣ የዳንኪራው ነገር... በአዳዲስ ባንዲራዎች አዳራሹ ደምቆ ሲታይ አቶ መለስ የዘራው አዝመራ እንዴቱን ያህል እንደጎመራ ከመቃብሩ ቀና ብሎ ቢመለከት ምንኛ በደስታ ይፈነጥዝ ያስብላል። ለማንኛውም ጃዋር መሀመድ እንኳን ደስ ያለው - ከአሸባሪነት የወጣበት ሰነድ የተፈረመበት ቀለም ገና ከመድረቁ የአንዲት ገናና ሀገርን ሰንደቅ ዓላማ ባስለወጠ ሁኔታ በዚህ መልክ "በሀገሩ" ያሻውን መሥራቱ ታሪካዊ ክስተት ነው - ወያኔ ጥቁር ውሻ ይውለድ!"ለዚህ ላበቃው" ቄሮ እንኳንስ በባዶ እግር ሄዶ ለሐውልት የመሠረት ድንጋይ ማኖር ይቅርና በጭንቅላቱም ቢሄድ ሲያንሰው ነው።

በነገራችን ላይ ይሄ ቄሮ ቄሮ የምትሉት ነገር ግራ እያጋባኝ መጥቶ አለ። የቄሮን ድርሻ በደምብ አውቃለሁ። ግሩም ሥራ ሠርተዋል - የኦሮሞ ወጣቶች። ነገር ግን እጅግ እየተጋነነ መጣና ድንበሩን ጣሰ። አንድ ነገር ደግሞ ድንበርን ሲጥስ የሚያስከትለው ጣጣ መኖሩ ሃቅ ነው - በቅጡ ያልተያዘ ድል ያነበርራል፤ አላግባብም ያሰክራል - በስካር ደግሞ መጃጃል አለ። የትዕቢትና ትምክህት መከሰት የመጀመሪያዎቹ በድል ስካር የመነብረር አሉታዊ ውጤቶች ናቸው። እነዚህ ነገሮች ደግሞ መሬትን እስክንጠየፍ ድረስ በኩራት አየር ላይ እንድንንሳፈፍና ሌላውን በዐይናችን ቂጥ እንድናይ ያደርጉናል። በዚህ ሂደት የመኳዛችን ጀብድ የሌሎች ሰዎችን ትንሽም ይሁን ትልቅ አስተዋፅዖና መስዋዕትነት አሳንሰን፣ የኛን ደግሞ ምትክ የሌለው ያህል አግዝፈን እንድናይ ያስገድደናል - በኢትዮጵያ የተፈጠረውም ይሄው ነው። "በላፐቶፕ መንግሥት ገለበጥኩ" የሚለን ጉደኛው ዶንኪሾትም ከዚህ በመነጨ ልዩ የድመት ትዕቢት ተገፋፍቶ ነው። በላፐቶፕ ያን ያህል ገድል መሥራት ስለመቻሉ አላውቅም ነበር። እንግዲያውስ የኮ/ል ደመቀ ትግል፣ የጎንደርና ጎጃም ትግል፣ የቆፍጣናዎቹ የጁዬዎችና የቃሉ የደሴ ትግል፣ የማጀቴና የወልቃይቶች ትግል፣ የራያና የሌላውም ሁሉ ትልና መስዋዕትነት ዋጋቢስ ነበር ማለት ነው - "በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደሰ" ማለት አሁን ነው ። የሆኖ ሆኖ እውነቱ ወደፊት ሲወጣ ሁሉም ማፈሩ አይቀርም። ግን ግን ፍቅርን በልክና በገደብ ማድረጉ ወደማይወጡት የስህተት አዘቅት ከመግባት ያድናል -

ለነገሩ ዋናው ድሉ እንጂ የድል ባለድርሻ ክፍፍል የትም አያደርስም። አሁንም ልድገመው - የቄሮ ድርሻ ትልቅ ነበር - ሀገርን በአንድ ኦነጋዊ አስተሳሰብ እስከመዳመጥ ሊያደርስ ግን አይችልም። እናም እየተስተዋለ ቢኬድ ቢያንስ የዚችን ደብዳቤ ልደት ማዘግየት ይቻል ነበር።ለነገሩ ሁን ያለው አይቀርምና እንዲህ የምብከነከነው በከንቱ ነው።

… ዝኮነ ኮይኑ መናገር ወደምፈልገው በቶሎ ላምራና ያን ተገላግዬ ወደ ንዴቴ ልመለስ።

በርካታ ትንቢቶችን አውቃለሁ - ይህ "ትንቢትን ማወቅ" ደግሞ የወፈፌዎች አንዱ መታወቂያቸው መሆኑን በእግረ መንገድ ማስታወስ እፈልጋለሁ። ብዙዎቹ ተፈጽመዋል። ጥቂቶችና መሠረታዊ የሚባሉት ይቀራሉ። ከሚቀሩት ውስጥ መረረንም ጎመዘዘንም ኢትዮጵያ ከነሙሉ ክብሯ ወደ ዝነኛ የታሪክ ሥፍራዋ በቅርብ የመመለሷ ዜና ነው። ይህን መጠራጠር ቶማስን መሆን ነው። ክርስቶስ ለቶማስ በጦር የተወጋ ቁስሉን በጣቱ እንዲዳብስና ከሞት መነሳቱን እንዲያምን ለመጠራጠሩ ዋጋ እንዲሆንም የነካበት ጣቱ እንዲጎነዲሽ አድርጓል። ቶማስ ክርስቶስ ሲነሳ አላየምና መነሳን ማመን አቅቶት ነበር። እኔን በመጠራጠሩ የሚጎዳ ሰው እንደማይኖር የምገልጸው ግን በታላቅ ትህትና ነው።

በገደምዳሜ የምለውን አትጠራጠሩ እያልኩ ነው። ኢትዮጵያ ትነሣለች። እንደሞተች የቀረችበት አንድም ዘመን የለም።

የሰሞኑ ግርግር የትንሣዔዋ ብሥራት መዳረሻ መስሎኝ ተጃጅዬ ሰውንም አጃጅዬ እንደነበር ልናዘዝ። ግን ይህ የሰሞኑ ህንፍሽፍሽ ለመጨረሻው ኢትዮጵያዊ አርማጌዴዎን የሚያመቻች የመሠሪዎች የጨረባ ተዝካር መሆን አለበት። በነፈሰው የምትነፍሱና የድርጅት አፈ ቀላጤ የሆናችሁ የሚዲያ አውታሮች ይህንን ጽሑፍ እንደማታወጡት ጠንቅቄ አውቃለሁ። እናንተን እንዲጥም ብዬ ግን እውነትን መሸፋፈን አልፈለግም። ከተለያዩ አቅጣጫዎች ያቀራሰምኩትን ሀገራዊ እውነት እናገራለሁ። የነገዎቹ የዴሞክራሲ ጠበቃዎች የዛሬዎቹ አፋኞች ደግሞ የሚጥማችሁን ሙዚቃ ብቻ እየመረጣችሁ ማዳመጣችሁን ቀጥሉ። በያለንበት ሰላሙን ያብዛለን።

"ለሦስት ወር ግፋ ካለም ለሦስት ዓመት ኢትዮጵያን የእስላም ንጉሥ ይገዛታል።" መባሉን ሰምቻለሁ። ያ ንጉሥ ጠ/ሚ ዶ/ር ዐቢይ አህመድ ይመስለኛል። ይህን ትንቢት እርሱም አያውቀው

ይሆናል። ወይም ያውቀውም ይሆናል። የስሙ መስተካከል ከዚህ ትንቢት ጋር ይገናኝ አይገናኝ አላውቅም። ግን ይህን ትንቢት አጠብቀው ነበርና አሁን ፍጻሜው ሳይሆን አይቀርም ብዬ እገምታለሁ። ሁኔታዎች ሁሉ እያቀጣጩ ያሉት በዚያ መስመር ነውና።

ከዚህ ዘመን ጋር - ከእስላሙ ንጉሥ ፍጻሜ ጋር - የሚያያዝ አንድ ነገር አለ። ያም ትልቅ ዕልቂት መኖሩ ነው። በዚያ ዕልቂት የሰው ዘር የተባለ አይተርፍም። በሩቅ የሚታይ ልብልብ ግንድ "ሰው ሳይሆን አይቀርም" ተብሎ በሰው ናፍቆት ወደዚያ ግንድ የሚሮጥበት ዘመን ይከሰታል። ከዚያ በኋላ ግን "የአንዲት ላም ወተትና የአንድ ማሣ ሰብል ላገር ይበቃል።" ረድዔትና በረከትም በሀገር ይናኛል። ክፋትና ምቀኝነት ይሰደዳሉ። የሰዎች ስደት ወደ ኢትዮጵያ ይሆናል። ይህ ዘመን ሊያልፍ ሲል ሁሉም በየቤቱ ሠይፍ ይስላል፤ ጥላቻና ያን የሚከተል መገዳደል የዘመኑ ፋሽን ይሆናል። ጥላቻ ይነግሣል፤ ፍቅር ይተናል፤ እናትና ልጅ፣ ወንድምና እህት ይናቆራሉ፤ ገንዘብ ይመለካል። ... ፐ! ትንቢት! የሚታየውን መናገር አሁን ትንቢት ነው?

ይህ የዶ/ር ዐቢይ ዘመን ያን ክፉ ትንቢት የሚያስቀር የመለኮት ጣልቃ ገብነት የታየበት መስሎኝ ነበር። ግን አይደለም። "ሰይጣን ለብልኃቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል" ይባላል። እናም የዚህ ልጅ አፍ አስከፊች ማራኪ ንግግር በቁሙ ሲመለከቱት እጅግ ግሩም ነው። ለአንድ ኖቤል ቀርቶ ለ30ም ቢታጭ ከድጋፍ በስተቀር ተቃውሞ የለኝም። ይሁንና ጉድና ጅራት ከወደኋላ እንደመሆኑ የቅርብ ጊዜ ሀገራዊ ሁኔታዎች እጅግ አደገኛና የጠ/ሚኒስትሩና ቡድኑ አካሄድ ዋጮን እንደመገልበጥ ሆኖ አይቼዋለሁ። ለደኅንነቴ ዋስትና የሚሰጠኝ ቢኖር በአደባባይ ብከራከር ደስ ባለኝ። ቢጨንቀኝ ወያኔዎች ጋር ለመነጋገርና አንዳች ሀገራዊ አስተዋፅዖ ላበረክት አሰብኩና ሥራቸው ፊቴ ላይ እየተደቀነ አንገሸገሸኝ። ያም እሳት፣ ይህም ዕጥፍ ድርብ እሳት።

ሀገራችን በሁለት እኩል አደገኛና እኩል ሰይጣናዊ አማራጮች መካከል ትገኛለች። አሁን ብዙው ሰው በሞቃት ንግግሮች ስለሰከረ እኔን ዕብድ የሚለው ወገን እንደሚበዛ በሚገባ አውቃለሁ። ለዚህ ነው ስጀምር ፍቅር ዕውር መሆኑን የተናገርኩት። እንደኔ ደግሞ

ይህን አዲስ ለውጥ ያፈቀረ ሰው አልነበረም። እውነቱ ግን ያ አይደለም። ሞራህን ግፈፍና ተመልከት!

በነገራችን ላይ ዐቢይን አሁንምና ወደፊትም አደንቃለሁ፤ ይህን ዓይነት ግለሰብ ለማግኘት ብዙ ትውልዶችን መጠበቅ እንደሚያስፈልግም እረዳለሁ። እኔ የምለው ግን ከእርሱም በላይ ስለሆነ ልዕለ-ሰብዓዊ ዕቅድና አፈጻጸሙ ነው። አትተርቡኝ። ነቢይም ሆነ ዐዋቂ አይደለሁም። ኢሕአፓን አስታውሱ፤ የምትመለምለው እንደኔ ያለውን ጀንፈልና እንደነዱሽ ሳይሆን ሲቻል ብልትን ሳይቻል ብልጡን ነበር።አንድ ኃይል - አወንታዊም ይሁን አሉታዊ - አካላዊም ይሁን መንፈሣዊ - ለሆነ ግዳጅ ከሰው ሰው ሲመርጥ የራሱ መለኪያ አለው- ከጊዜውና ከሁኔታዎች ጋር የሚሄድ ሰው ያዘጋጃል እንጂ በቀላሉ የሚንበረከክ ሰው አይመርጥም። መሬት ለነከሰ ጥልቅ ምሥጢር ላለው ዓላማ የሚመረጡ ሰዎች በብዙ መንገድ የማያሳሙ እንዲሆኑ አስፈላጊ ነው - ለምሣሌ 33 ዲግሪ ኢሉሚናቲ ለመድረስ ብዙ መፍጋ አለብህ፤ እንደቁጩው የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ሳይሆን ባደጉ አገሮች ጄኔራል ለመድረስ ብዙ ውጣ ውረድ እንዳለው ማለት ነው። ቀጥሎ የሚሆነውን እኮ ራሱ ዐቢይም "እኔ የምረዳውን" ያህል እንኳን ላያውቅ ይችላል። ዓለም በራሷ ከባድ ምሥጢር ናት።… ዶ/ር ዐቢን ግን አሁንም ወደፊትም ከልቤና በጣም እንደምወደው መግለጽ እፈልጋለሁ። ችግሩ የችግሮቻችን ጥልቀት ከጣፋጭ ንግግርና ከአስለምላሚ ትክለ-ሰውነታዊ መስህብ የገዘፉ በመሆናቸው አህያን ተከልለው ለሚመጡ ጅቦች የመጋለጣችን ዕጣ የማይቀርልን መሆኑ ነው፤ ችግሩ ኢትዮያን ከሚጠሉ ጅቦች ኢትዮጵያን ከነጭርሱ ወደማያውቁ ድቦች የመሸጋገሪያ ምዕራፍ ላይ መገኘታችን ነው፤ ትልቁ ችግር በሲዖል ውስጥ እንኳን ጥቂት ዕረፍት ሲኖር እኛ ግን ካለምንም ዕረፍትና እፎይታ (የሦስት ወር የማገገሚያ ጊዜ እንደረፍት ካልተቆጠረ በስተቀር) ከአንዱ የስቃይ ዐውድ ወደ ሌላው መተላለፋችን ነው። የምለው ሁሉ ውሸት ቢሆን በወደድኩ - ግን አይሆንም። በምኞት የቀረ የትንቢት ፍጻሜ የለም - ምናልባት የአደጋውን መጠን መቀነስና ጊዜውን ማዛወር ይቻል እንደሆነ እንጂ። እኛም በርትተን እንጸልይ - ማን ያውቃል - አንድዬ ሊያለዝብልን ይችላል።

አንድም ጦር የሌለውን ዳውድ ኢብሣን ለመሸምገልና ከእነግ ጋር ለመደራደር የአንዲት ትልቅ ሀገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና

የአንድ ትልቅ ክልል ፕሬዝደንት አሥመራ ድረስ መሄዳቸው ምን ማለት ነው? ምን እየተጠነሰሰልን ይሆን? ጦር ሠራዊቱ የት እንዳለ እንኳን የማይታወቅ በጥቂት ግለሰቦች የወሬ ቱማታ ብቻ ሕይወት ያለው የሚመስልን የግማሽ ምዕተ ዓመት ዕድሜ ባዶ ድርጅት ነፍስ እንዲዘራና ባንዲራው ወይም ዓርማው የሀገራችንን ባንዲራ ረጋግጦ መናገሻ ከተማ ውስጥ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ እየተደረገ ያለው በምን ምክንያት ይሆን?እንደዚያ ከሆነ ኢሕአፓንም ጦሩን አስፈትቶ ወደ ሀገር ለማምጣት ለምን አይሞክሩም? ማዕከላዊ መንግሥትን በኦነግ የመሙላቱ ሂደትስ ምን አመላካች ነው? አለ ነገር! ወያኔዎች ግን ጥቁር ውሻ ውለዱ! በናንተ ቤት ኢትዮጵያን ገድላችኋል። ኢትዮጵያን የጎዳችሁ መስሏችሁ ወደ አራት ሚሊዮን የሚገመቱ ተጋሩን ነው ልታሳርዱ የተዘጋጃችሁት - በመላዋ ኢትዮጵያ። አማራ ብቻ የሚታረድ መሰላችሁ አይደል? አማራማ ወያኔን ምሥጋን ይንሳውና መኮላሸቱንም፣ መዋረዱንም፣ መታሰሩንም ፣ መገደሉንም፣ መታረዱንም፣ መሰደዱንም፣ … ለምዶታል። እነዚህ ነገሮች ከእንግዲህ እንደብርቅ እየታዩ ኋላ ላይ ግን የሚለመዱት በወያ መንደር ውስጥ ነው። ያለዘሩት አይበቅልም፤ ያልተከሉት አይጠድ። ወዩዬ ለአማራ የዘራሸው የመከራ እንክርዳድ ላንቺም መጥቷልና ዝግጁ ሆነሽ ጠብቂ። አዎ፣ እያንዳንድሽ የወያኔ አባል ባለፉት 27 ዓመታት በተለይ በአማራው ላይ የሠራሽው ተነግሮ የማያልቅና ሊነገርም የሚዘገንን ግፍና በደል በራስሽ ወይ በልጅሽ አሊያም በዘርሽ ትከፍያታለሽ! አማራና ትግሬን ለስታርቅ እልና ደግሞ … ሆ… እንኳን እኔ ደካማው ፍጡር እግዚአብሔር ራሱም የሚችል አይመስለኝም። እንዴ - ጭካኔቸው ጭካኔ ነው እንዴ? ይመችህ ጃዋር! በአክራሪ ጎሠኛነትህ ላይ አክራሪ ሙስሊምነት ተደርቦበት ጉድ ልናይ ነው ከእንግዲህ። ለኔ ዓይነቱማ አንድ ሣይሆን ሃምሣ ሜንጫ ነው የምታሰልፍልኝ። ገና ከአሁኑ 12 ቤተ ክርስቲያን ተቃጥሏል፤ በርካታ ካህናት ጋይተዋል፤ ብዙ ምዕመናን ተገድለዋል፤ … በዚህ አካሄዳችን ከቀጠልን በጥቂት ወራት ውስጥ ከምድረ ገፅ የመጥፋት ተስፋ አለን። በተስፋ ውስጥ ደግሞ ሌላም ተስፋ አለ ታዲያ። የቄራ ዐውድማው ተለቅልቋል፤ አራጆቹም ከያቅጣጫው በመጠራራት እየተሰባሰቡ ነው። ጠላታቸውንም ለይተዋል። እስኪጠናከሩና ገዢ መሬት እስኪይዙ ጥሩ የንግግር ችሎታ ያለውን ሰው መድበዋ። በኋላ ግን ይፈገልቱትና

*የመጨረሻውን ዙር የዕልቂት እምቢልታ ይነፋሉ፤ አዲዮስ! ወያኔዎች ጥቁር ውሻ ውለዱ!! ጥሩ ሀገር የመሥራት ዕድል እያላችሁ ጥሩ ኦሽትዊዝ ገነባችሁልን። ደግነቱ ከሞት የሚቀር የለም። (በሉ - በዚህ አጋጣሚ ፊንፊኔ ላይ አንዲት ኩሽና ቢጤ ስላለችኝ የሚገዛኝ ሰው ፈልጉልኝና እኔም በተራዩ ጂጂጋ ወደሸገር ከመምጣቷ በፊት እግሬ ባመራኝ ልፈትለክ…።) (ረስቼ - ያ ፀጋዩ አራርሳ የሚሉት ገልቱ የወያኔና ኦነግ የፕሮፓጋንዳ ሰለባ በእንግሊዝኛ ተናገረ አሉ? እሰይ! እንኳን በንግሊዝ አፍ ተናገረ - ማንን ደስ ይበለው? ማንንስ ይከፋው? በማንነት ጥያቄ እየቃተቱ የማንም ሳይሆኑ እንደማርጀት ያለ የከፋ ችግር የለም። ኦሮሚፋን ግን በቶሎ ይማር።)*

*ከፍ ሲል እንደጠቀስኩት ወያኔ ባሏን የጎዳች መስሏት ሰውነቷን በጋሬጣ እንደወጋችው ሴት ናት። ወያኔ ኢትዮጵያን ያቃለለች መስሏት፣ ወያኔ "ሀገሪቱ" እያለ ስሟን እንኳን ለመጥራት ተጠይፎ ለማትወጣው የችግር አረንቋ አጋልጧት የሄደውን የቀድሞ ጠ/ሚኒስትር ሌጋሲ ለማስፈጸም ስትል…. ኤዲያ ምን አስለፈ…።*